

**የእጩ ስም:-** **Julie Kang (ጁሊ ካንግ)**
**የምርጫ ዘመቻ ስም:-** **Julie for Seattle D5 (ጁሊ ለሲያትል D5)**
**የምርጫ ዘመቻ ድህረ ገጽ:-** **https://julieforseattle.com/**
**የሥራ መደብ:-** **የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት 5**
**የምርጫ ዘመቻ ስልክ ቁጥር:-** **206.880.3873**
**የእጩ መተዋወቂያ (የ200 ቃላት ገደብ):-**

የዲስትሪክት 5 የረጅም ጊዜ ነዋሪ፣ አስተማሪ፣ እና ንቁ የማህበረሰብ አባል ነኝ። በሰሜን ሲያትል ህይወቴን የገነባሁ ስደተኛ እንደመሆኔ መጠን፣ የከተማ ውሳኔዎች የሠራተኛ ቤተሰቦችን፣ ስደተኞችን፣ እና አነስተኛ ንግዶችን የዕለት ተዕለት ተግባራትን እንዴት እንደሚቀርጹ ተረድቻለሁ።

መሪዎቻችን እንዲያዳምጡን እና ዲስትሪክታችን በትክክል ምን እንደሚፈልግ እንዲረዱ እንፈልጋለን። ቅድሚያ የምሰጣቸው ነገሮች በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት መቻል፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መኖሪያ ቤት፣ ደህንነት፣ እና ቤት አልባነት እና የስደተኞች ጥበቃዎች ናቸው።

ሙያዊ ሕይወቴን በሕዝብ እና በከፍተኛ ትምህርት አሳልፌያለሁ፣ ባለብዙ ቋንቋ ተማሪዎችን ለመደገፍ መምህራንን አሰልጥኛለሁ። በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዋሽንግተን እና በሲያትል ዩኒቨርሲቲ ሠርቻለሁ፣ ትላልቅ ፕሮግራሞችን በመምራት እና በመንደፍ፣ ውስብስብ የህዝብ በጀቶችን በማስተዳደር፣ እንዲሁም በተጠያቂነት፣ በፍትሃዊነት፣ እና በውጤቶች ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የዘርፍ ሽርክናዎችን በመገንባት።

በሃለር ሌክ ማህበረሰብ ክለብ ቦርድ ውስጥ አገለግላለሁ፣ በምግብ ባንክ ውስጥ በፈቃደኝነት እሠራለሁ፣ ስደተኞች ማህበረሰባችንን አስተምራለሁ እና ህብረተ-ሰቡን ከ ICE በፊሽካ እና በሌሎች ነገሮች ለማንቃት እሰራለሁ፣ እና አነስተኛ ንግዶችን ለመደገፍ የFuseD5 የእግር ጉዞዎችን እመራለሁ። የWEA ዩኒየን ኩሩ አባል ነኝ እንዲሁም ባለቤቴ የUFCW 3000 አባል ነው።

ለከተማችን ምክር ቤት የማህበረሰብ እውቀትን፣ የባንክ ልምድን፣ የፖሊሲዎች እውቀትን እና አስተማማኝ አመራርን ይዤ እመጣለሁ። ማህበረሰባችን የሚፈልገው ዓይነት መሪ ለመሆን ቃል እገባለሁ - ድምጽ ለሌላቸው ሰዎች የምታዳምጥና የምትሟገት ሰው።

የእርስዎን ድጋፍ ለማግኘት እና ዲስትሪክታችንን ለመወከል ክብር ይሰማኛል።

*ይህች እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ ተሳታፊ ናት።*



**የዕጩ ስም:-** Silas James (ሳይለስ ጀምስ)

**የምርጫ ዘመቻ ስም፦**ሳይለስ ለሲያትል (Silas for Seattle)

**የምርጫ ዘመቻ ድረ ገጽ:-** https://silasforseattle.com/

**ለከተማው የሚወዳደሩበት   የሥራ መደብ:-** City Council District 5 (የ ዲስትሪክት 5 የከተማ ምክር ቤት)

**የምርጫ ዘመቻ ስልክ ቁጥር:-** (425) 224-5463

እኔ Silas James እባላለሁ፣ ከተማችን ለሁሉም ሰው በተሻለ ሁኔታ እንድትሠራ ለማድረግ በDistrict 5 የSeattle City Council አባል ለመሆን ዕጩ ሆኜ ቀርቤያለሁ። እንደ አንድ አካል ጉዳተኛ አስተማሪ፣ ተመራማሪ፣ ተሚጋች እና የ Seattle Disability Commission (የሲያትል የአካል ጉዳተኞች ኮሚሽን) ሰብሳቢ፣ በተበላሹት ሥርዓቶቻችን ተስፋ ቆርጫለሁ። ሀብታም ኮርፖሬሽኖች ተገቢውን ድርሻ እንዲከፍሉ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች እንዲስፋፉ፣ እንዲሁም በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ የደህንነትና ለአየር ንብረት ፍትህ የሚረዱ መፍትሄዎች እንዲፈጠሩ ለማድረግ በቁርጠኝነት እና በትጋት እሰራለሁ። አቅመ ደካማ ለሆኑ ጎረቤቶቻችን የምትመች Seattleን መፍጠር ከቻልን፣ ሁላችንም ተጠቃሚ እንሆናለን። በጣም ተጋላጭ ለሆኑ ጎረቤቶቻችን የሚሠራ ሲያትል ከፈጠርን ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናል።

አብዛኛውን የሕይወት ዘመኔን የመንግሥት ድጋፎችን (Public benefits) በመጠቀም ያሳለፍኩ ሲሆን፣ በዚህም ልምዴ ስለ እነዚህ ውስብስብ ሥርዓቶች ከፍተኛ ክህሎት ያካበትኩ ባለሙያ ሆኛለሁ። ግለሰቦችን በመምራትና ቡድኖችን በማስተማር ስኬታማ እንዲሆኑ ስረዳ የቆየሁ ቢሆንም፣ አሁን ግን ለመላው Seattle የሚተርፍ ጥቅም ለማስገኘት መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥን ለማምጣት ቆርጬ ተነስቻለሁ።

ሰዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያስፈልጋቸውን ግብአቶች ለማቅረብ እንዲሁም ማንነታቸው፣ መገኛቸው ወይም ያላቸው የገንዘብ መጠን ሳይለይ ሰፈሮቻችን ለሁሉም ደኅንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆኑ ለማድረግ በዚህ ምርጫ እወዳደራለሁ።

የዲሞክራሲ ቫውቸሮችዎን (Democracy Vouchers) ለSilas for Seattle በመስጠት ለዘመቻዬ ድጋፍ እንዲያደርጉልኝ እጠይቃለሁ። የከተማችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የእኛ እንጂ የቢሊየነር ኮርፖሬሽኖች አለመሆኑን ያረጋግጡ።

*ይህ ዕጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።*